# ሥራ ፡ ለማቋረጥ ፡ የማይችሉ ፡ ሠራተኞች ።

## ከሮበርት ፡ ሲ ፡ ሚንስ ።

ስለ ፡ አሠሪና ፡ ሠራተኞች ፡ ጉዳይ ፡ የወጣው ፡ አዋጅ ፡ [1] በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ ላሉት ፡ አብዛኞቹ ፡ ሠራተኞች ፡ ሥራን ፡ የማቋረጥ ፡ መብት ፡ ሰጥቷቸዋል ፡ ወይም ፡ መብቱን ፡ እንደነበረ ፡ ጠብቆላቸዋል ። በአዋጁ ፡ መሠረት ፡ ይህ ፡ መብት ፡ ያልተወሰነ ፡ አይደለም ። በዚህ ፡ መብት ፡ ሊጠቀም ፡ የሚችለው ፡ የሠራተኛ ፡ ማኅበር ፡ ብቻ ፡ ሲሆን ፡ [2] የሥራው ፡ ክርክር ፡ ቢያንስ ፡ ከስድሳ ፡ ቀናት ፡ በፊት ፡ ለአሠሪና ፡ ሠራተኛ ፡ ጉዳይ ፡ ቦርድ ፡ ካልቀረበ ፡ በስተቀር ፡ [3] የሠራተኛ ፡ ማኅበርም ፡ እንኳን ፡ በመብቱ ፡ ሊጠቀምበት ፡ አይችልም ። ሆኖም ፡ ምንም ፡ እንኳን ፡ የሥራ ፡ ማቋረጥ ፡ መብት ፡ በነዚህና ፡ በሌሎችም ፡ ሁኔታዎች ፡ ቢወሰንም ፡ አዋጁ ፡ በአሠሪና ፡ በሠራተኞች ፡ መካከል ፡ ላለው ፡ ግንኙነት ፡ ሥራ ፡ ማቋረጡን ፡ የሠራተኞች ፡ ተገቢ ፡ መሣሪያ ፡ አድርጎ ፡ በጠቅላላው ፡ ያውቅለታል ።

ይህ ፡ ጠቅላላ ፡ መሠረተ ፡ ሐሳብ ፡ የማይመለከታቸው ፡ ሁለት ፡ ዋና ፡ ዋና ፡ የሠራተኛ ፡ ጓዶች ፡ አሉ ። የመጀመሪያው ፡ "የመንግሥት ፡ ሠራተኞች" ፡ ሲሆን ፡ "የመንግሥት ፡ ሠራተኞች" ፡ የተሰኘው ፡ ሐረግ ፡ ሲተረጐም ፡ ትርፍ ፡ በሚያስገኙ ፡ የሥራ ፡ ድርጅቶች ፡ ከሚሠሩት ፡ በስተቀር ፡ በጠቅላላው ፡ ሌሎችን ፡ በመንግሥት ፡ የተቀጠሩ ፡ ሠራተኞችን ፡ ሁሉ ፡ ያጠቃልላል ። ሁለተኛው ፡ እንደማመላለሻና ፡ የመብራት ፡ ኃይል ፡ በመሰሉት ፡ የሕዝብ ፡ አገልግሎቶች ፡ በሚሰጡ ፡ የሥራ ፡ ድርጅቶች ፡ ውስጥ ፡ ያሉ ፡ ሠራተኞች ፡ ናቸው ።

### የመንግሥት ፡ ሠራተኞች ።

የመንግሥት ፡ ሠራተኞች ፡ አቋም ፡ በቀላሉ ፡ እንደሚከተለው ፡ ሊገለጽ ፡ ይቻላል ፦ በማናቸውም ፡ ሁኔታ ፡ ቢሆን ፡ ሥራ ፡ ለማቋረጥ ፡ አይችሉም ። ይህ ፡ ክልከላ ፡ ዋና ፡ የሆኑ ፡ የሕግ ፡ ጭብጦች ፡ አያስነሳም ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ስለ ፡ ክልከላው ፡ የሚመለከቱትን ፡ ደንቦች ፡ መመርመር ፡ ስለ ፡ አሠሪና ፡ ሠራተኛ ፡ ጉዳይ ፡ አዋጅ ፡ አቋምና ፡ በአዋጁም ፡ ውስጥ ፡ ስላሉት ፡ አያሌ ፡ ትርጓሜዎች ፡ ጠቃሚ ፡ ማብራሪያ ፡ ይሰጣል ።

አዋጁ ፡ ራሱ ፡ በመንግሥት ፡ ሠራተኞች ፡ የሚደረግ ፡ የሥራ ፡ ማቋረጥን ፡ አይከለክልም ። አዋጁ ፡ የመንግሥት ፡ ሠራተኞችን ፡ ከ"ሠራተኛ" ፡ ትርጓሜ ፡ ውጭ ፡ ያደርጋቸዋል ። "ሠራተኛ" ፡ የሚለው ፡ ቃል ፡ "የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ በ፪ሺ፭፻፲፪ኛው ፡ አንቀጽ ፡ እንደ ፡ ተመለከተው ፤ የሥራ ፡ ውል ፡ የገባ ፡ ማናቸውም ፡ ሰው ፡ ማለት ፡ ነው" ፡ ሲል ፡ አንቀጽ ፡ ፪(ረ) በጠቅላላ ፡ አነጋገር ፡

---

1. የ፲፱፻፶፮ ፡ ዓ ፡ ም ፡ አዋጅ ፡ ቍጥር ፡ ፪፻፲ ፡ ነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፡ ፳፫ኛ ፡ ዓመት ፡ ቍጥር ፡ ፫ ፡ ሕጉ ፡ ቀድሞ ፡ እንደ ፡ ንጉሡ ፡ ነገሥታዊ ፡ ድንጋጌ ፡ ወጥቶ ፡ ነበር ፤ የ፲፱፻፶፬ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ድንጋጌ ፡ ቍጥር ፡ ፵፱ ፡ ነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፡ ፳፩ኛ ፡ ዓመት ፡ ቍጥር ፡ ፲፰ ። በሚቀጥለው ፡ ዓመት ፡ ምክር ፡ ቤቱ ፡ ከጥቂት ፡ ማሻሻያዎች ፡ ጋር ፡ አጽድቆት ፡ አዋጁ ፡ ቍጥር ፡ ፪፻፲ ፡ ተብሎ ፡ እንደገና ፡ ታተመ ።
2. አንቀጽ ፡ ሁለት ፡ ደ ፡ ፩(፱) (ሀ) ፡ የሌላ ፡ ሆነው ፡ ካልተገለጹ ፡ በስተቀር ፡ የግርጌ ፡ ማስታወሻዎች ፡ ሁሉ ፡ የሚመለከቱት ፡ ስለ ፡ አሠሪና ፡ ሠራተኛ ፡ ጉዳይ ፡ የወጣውን ፡ አዋጅ ፡ ነው ።
3. አንቀጽ ፡ ሁለት ፡ ደ ፡ ፩(፪) (መ) ።

ይገልጸዋል ። ሆኖም ፡ ምንም ፡ እንኳን ፡ ሥራቸውን ፡ በሥራ ፡ ውል ፡ መሠረት ፡ ቢያከናውኑም ፡ ለአዋጁ ፡ አፈጻጸም ፡ ሲባል ፡ እንደሠራተኞች ፡ የማይቆጠሩ ፡ አራት ፡ የልዩ ፡ ልዩ ፡ ተግባር ፡ ጓዶች ፡ ከጠቅላላው ፡ ትርጓሜ ፡ ቀጥሎ ፡ ተዘርዝረዋል ፡ እነዚህም ፡ ሥራ ፡ አስኪያጆች ፡ የቤት ፡ አሽከሮች ፡ ከአሥር ፡ የሚያንሱ ፡ ቀዋሚ ፡ ሠራተኞች ፡ በሚገኙበት ፡ እርሻ ፡ ውስጥ ፡ የሚሠሩ ፡ ሠራተኞችና ፡ የመንግሥት ፡ ሠራተኞች ፡ ናቸው ።

ስለ ፡ አሠሪና ፡ ሠራተኞች ፡ ጉዳይ ፡ የወጣው ፡ አዋጅ ፡ “ሠራተኛ” ፡ በሚለው ፡ ቃል ፡ ደጋግሞ ፡ ቢጠቀምበት ፡ ምንም ፡ አያስደንቅም ። አዋጁ ፡ የሚመለከተው ፡ በጠቅላላው ፡ ስለ ፡ ምጣኔ ፡ ሀብት ፡ (ኤኮኖሚክ) ፡ ግኑኙነት ፡ ሳይሆን ፡ በአሠሪዎችና ፡ በሠራተኞች ፡ መካከል ፡ ስላለው ፡ የምጣኔ ፡ ሀብት ፡ ግንኙነት ፡ ብቻ ፡ ነው ። ስለዚህም ፡ ሠራተኞች ፡ በሆኑትና ፡ ባልሆኑት ፡ ሰዎች ፡ መካከል ፡ ያለው ፡ ልዩነት ፡ መሠረታዊ ፡ ነው ፤ የሚከተለውም ፡ ውይይት ፡ የአዋጁን ፡ ረቂቅ ፡ ያዘጋጁት ፡ ሰዎች ፡ “ሠራተኛ” ፡ የሚለውን ፡ ቃል ፡ የሚጠቀሙበት ፡ በሰጡት ፡ ትርጓሜ ፡ መሠረት ፡ ነው ፡ በሚል ፡ እምነት ፡ መመሥረቱን ፡ አጥብቆ ፡ ማስገንዘብ ፡ መልካም ፡ ነው ። በሌላ ፡ አነጋገር ፡ አዋጁ ፡ “ሠራተኞች”ን ፡ መብት ፡ ሲሰጣቸው ፡ ወይም ፡ ግዴታ ፡ ሲጥልባቸው ፡ ይህን ፡ የሚያደርገው ፡ በአንቀጽ ፡ ፪(ረ) ፡ ሠራተኛ ፡ በሚለው ፡ ትርጓሜ ፡ ስር ፡ ለተጠቃለሉ ፡ ሰዎች ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ ተብሎ ፡ ይታመናል ።

ከዚህ ፡ አስቀድመን ፡ አራት ፡ የልዩ ፡ ልዩ ፡ ተግባር ፡ ጓዶች ፡ ከአንቀጽ ፡ ፪(ረ) ፡ ትርጓሜ ፡ ውጭ ፡ ናቸው ፡ ብለናል ። ከትርጓሜው ፡ ውጭ ፡ መሆናቸው ፡ ከሚያስከትለው ፡ ሕጋዊ ፡ ውጤቶች ፡ እዚህ ፡ ላይ ፡ የምንመለከተው ፡ ሁለቱን ፡ ነው ። በመጀመሪያ ፡ አዋጁ ፡ ማኅበርን ፡ “ሠራተኞች . . . አባል ፡ የሆኑበት ፡ ድርጅት ፡ ማለት ፡ ነው” [4] ብሎ ፡ ትርጓሜ ፡ ስለሚሰጠው ፡ እነዚህ ፡ ሰዎች ፡ የሠራተኛ ፡ ማኅበር ፡ ሊያቋቁሙ ፡ አይችሉም ። የመንግሥት ፡ ሠራተኞችና ፡ ሌሎችም ፡ ከአንቀጽ ፡ ፪(ረ) ፡ ወጭ ፡ የተተወት ፡ ጓዶች ፡ ከአሠሪዎቻቸው ፡ ጋር ፡ የሚነጋገርላቸውን ፡ ድርጅት ፡ ከማቋቋም ፡ ስለ ፡ አሠሪና ፡ ሠራተኛ ፡ ጉዳይ ፡ የወጣው ፡ አዋጅ ፡ አያግዳቸውም ፤ [5] ነገር ፡ ግን ፡ ማንኛውም ፡ የሚያቋቁሙት ፡ ድርጅት ፡ ለአዋጁ ፡ አፈጻጸም ፡ እንደ ፡ ሠራተኛ ፡ ማኅበር ፡ አይቆጠርም ። ስለዚህም ፡ አዋጁ ፡ ሥራ ፡ ማቋረጥን ፡ ለሠራተኛ ፡ ማኅበሮች ፡ ብቻ ፡ ስለሚፈቅድ ፡ እነዚህ ፡ ጓዶች ፡ ውስጥ ፡ ያሉት ፡ ሰዎች ፡ ሥራቸውን ፡ ቢያቋርጡ ፡ አድራጎቱ ፡ በአዋጁ ፡ መሠረት ፡ ሕገ-ወጥ ፡ ይሆናል ።

ሁለተኛ ፡ በሌላው ፡ በኩል ፡ “ሥራ ፡ ማቋረጥ” ፡ በአዋጁ ፡ በተለይ ፡ ትርጓሜ ፡ የተሰጠው ፡ ቃል ፡ ነው ። ሥራ ፡ ማቋረጥ ፡ “ብዙ ፡ ሠራተኞች ፡ ለጊዜው ፡

---

4፤ አንቀጽ ፡ ሁለት ፡ በ ፡

5. ሠራተኞች ፡ እንደማንኛውም ፡ ሰው ፡ ሕጋዊ ፡ የሆነ ፡ የኅብረት ፡ ጥቅም ፡ ለማግኘት ፡ ማኅበሮች ፡ ለማቋቋም ፡ በጠቅላላው ፡ ነጻ ፡ ናቸው ፤ ቢያንስ ፡ አንድ ፡ የሠራተኞች ፡ ማኅበር ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሠራተኞች ፡ ማኅበር ፡ በ፲፱፻፶፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡ (በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ደንቦች ፡ መሠረት) ፡ በአገር ፡ ግዛት ፡ ሚኒስቴር ፡ ተመዝግቧል ፤ ይህም ፡ የሆነው ፡ ስለ ፡ አሠሪና ፡ ሠራተኛ ፡ ጉዳይ ፡ አዋጅ ፡ ከመውጣቱ ፡ አንድ ፡ ዓመት ፡ አስቀድሞ ፡ ነው ። አር ፡ ስትትዝ ፡ ዘ ፡ ዲቨሎፕሜንት ፡ ኦፍ ፡ ሌበር ፡ ሌጅስሌሽን ፡ ኢን ፡ ኢትዮፒያ ፡ (ያልታተመ) ። አዋጁ ፡ ከወጣ ፡ በኋላ ፡ ሠራተኞች ፡ በአዋጁ ፡ ስር ፡ “የሠራተኛ ፡ ማኅበር” ፡ የሆነ ፡ ማኅበርን ፡ ብቻ ፡ ሊያቋቁሙ ፡ ይችላሉ ፡ ብሎ ፡ መከራከር ፡ ይቻላል ። ሆኖም ፡ ይህን ፡ ዓይነት ፡ መደምደሚያ ፡ ከአዋጁ ፡ መውሰድ ፡ ተገቢ ፡ መሆኑ ፡ በጣም ፡ አጠራጣሪ ፡ ነው ፤ ያም ፡ ሆነ ፡ ይህ ፡ በአዋጁ ፡ ውስጥ ፡ ከሠራተኛ ፡ ትርጓሜ ፡ በመገለሳቸው ፡ ከአዋጁ ፡ ውጭ ፡ የሆኑትን ፡ ሠራተኞች ፡ መመልከት ፡ አይገባውም ።

ተስማምተው ፡ የሚያደርጉት ፡ የሥራ ፡ ማቋረጥ ፡ ማለት ፡ ነው ።" [6] (አንክሮው ፡ የተጨመረ ፡ ነው) ፡ ከአንቀጽ ፡ ፪(ረ) ፡ ትርጓሜ ፡ ውጭ ፡ የሆኑት ፡ የሥራ ፡ ጓዶች ፡ "ሠራተኞች" ፡ ስላልሆኑ ፡ በነሱ ፡ በኩል ፡ በስምምነት ፡ የሚደረግ ፡ ማናቸውም ፡ የሥራ ፡ ማቆም ፦ በተራ ፡ አነጋገር ፡ ሥራ ፡ ማቋረጥ ፡ ተብሎ ፡ የሚጠራው ፦ በአዋጁ ፡ አተረጓጐም ፡ ሥራ ፡ ማቋረጥ ፡ አይደለም ፤ በአዋጁም ፡ ስለ ፡ ሥራ ፡ ማቋረጥ ፡ የተደነገጉት ፡ ማናቸውም ፡ ገደቦች ፡ ተፈጻሚነት ፡ የላቸውም ። በተለይም ፡ ከሠራተኛ ፡ ማኅበር ፡ ሌላ ፡ ሥራ ፡ ማቋረጥን ፡ ቢያዘጋጅ ፡ ሕገ-ወጥ ፡ ይሆናል ፡ የሚለውን ፡ ደንብ ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ ለማዋል ፡ አንዳችም ፡ ምክንያት ፡ የለም ። እነ ዚህን ፡ ከ"ሠራተኛ" ፡ ትርጓሜ ፡ ውጭ ፡ የተተውትን ፡ አራት ፡ ጓዶች ፡ የወሰ ድን ፡ እንደሆን ፡ ስለ ፡ አሠሪና ፡ ሠራተኛ ፡ ጉዳይ ፡ የወጣው ፡ አዋጅ ፡ በብዙ ፡ ረገድ በጭራሽ ፡ እንዳልወጣ ፡ ይቆጠራል ። በሠራተኛ ፡ አቋም ፡ ላይ ፡ በቀጥታ ፡ ወይም ፡ በተዘዋዋሪ ፡ መንገድ ፡ የተመሠረተ ፡ የአዋጁ ፡ ደንብ ፡ በእነርሱ ፡ ላይ ፡ ምንም ፡ ውጤት ፡ የለውም ።

ሆኖም ፡ ከአዋጁ ፡ ከአብዛኞዎቹ ፡ ደንቦች ፡ ክልል ፡ ውጭ ፡ መውገዳቸው ፡ ለመንግሥት ፡ ሠራተኞች ፡ የሚያስከትለው ፡ ውጤት ፡ ለሌሎች ፡ ከትርጓሜው ፡ ውጭ ፡ ለተተውት ፡ ጓዶች ፡ ከሚያስከትለው ፡ ውጤት ፡ ጋር ፡ አንድ ፡ አይደለም ። ለሌሎች ፡ የሚያስከትለው ፡ ውጤት ፡ የአሠሪንና ፡ የሠራተኛን ፡ ግንኙነት ፡ በሚ መለከቱት ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቍጥሮች ፡ ውስጥ ፡ መተውን ፡ ነው ። [7] ከነ ዚህም ፡ ቍጥሮች ፡ አንዱ ፡ ብቻ ፡ ቍጥር ፡ ፪ሺ፭፻፸፮ ፡ በሥራ ፡ ማቋረጥ ፡ መብት ፡ ላይ ፡ ሕጋዊ ፡ ወሰኖችን ፡ ይደነግጋል ። ቍጥሩም ፡ እንደሚከተለው ፡ ነው ፤

፩ ፤ ላንድ ፡ የሥራ ፡ ማቆም ፡ አድማ ፡ የሠራተኛው ፡ ተካፋይ ፡ መሆን ፡ የሥራ ፡ ማቆም ፡ አድማ ፡ የተደረገው ፡ አሠሪውን ፡ ለመጉዳት ፡ ብቻ ፡ የሆነ ፡ እንደሆነ ፡ ወይም ፡ በሕግ ፡ ወይም ፡ በሕዝብ ፡ ባለሥልጣኖች ፡ የተከለከለ ፡ የሆነ ፡ እንደሆነ ፡ ውሉን ፡ ለማፍረስ ፡ ለአሠሪው ፡ ትክክለኛ ፡ ምክንያት ፡ ይሆናል ።

፪ ፤ ከነዚህ ፡ ሁኔታዎች ፡ ውጭ ፡ የሥራ ፡ ማቆም ፡ አድማ ፡ ውሉን ፡ ለማፍ ረስ ፡ ትክክለኛ ፡ ምክንያት ፡ አይሆንም ።

በቍጥር ፡ ፪ሺ፭፻፸፮(፩) ፡ የተደነገገው ፡ ወሰን ፡ ብዙ ፡ የሚከለክል ፡ አይደ ለም ። ቍጥሩ ፡ ተፈጻሚ ፡ ከሚሆንባቸው ፡ ሦስት ፡ ሁኔታዎች ፡ ሦስተኛው ፡ ብቻ ፡ ማለት ፡ የሥራ ፡ ማቆም ፡ አድማው ፡ በሕዝብ ፡ ባለሥልጣኖች ፡ ዘንድ ፡ የተከለ ከለ ፡ እንደሆነ ፡ የሚለው ፡ በተግባር ፡ ላይ ፡ የሚውል ፡ ጠቃሚነት ፡ ሊኖረው ፡ ይችላል ። ሠራተኞች ፡ አሠሪያቸውን ፡ ለመጉዳት ፡ ብቻ ፡ ሲሉ ፡ ሥራ ፡ ቢያቆሙ ፡ ይህን ፡ የሚያደርጉባቸው ፡ ጊዜያት ፡ በጣም ፡ ጥቂት ፡ ናቸው ፤ በሥራ ፡ ማቋረጣ ቸው ፡ ምክንያት ፡ በአሠሪያቸው ፡ ላይ ፡ የሚደርሰው ፡ ጉዳት ፡ አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡

---

6. አንቀጽ ፡ ሁለት ፡ ሀ ።

7. አንድ ፡ የተለየ ፡ ሥራ ፡ ማቋረጥ ፡ በዓላማው ፡ ወይም ፡ ሥራ ፡ ያቋረጡት ፡ በወሰዱት ፡ እርምጃ ፡ በኩባንያ ፡ ንብረት ፡ ላይ ፡ ጉዳት ፡ እንደ ፡ ማድረስ ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ቍጥር ፡ ፫፻፺፬ ፡ ምክንያት ፡ ሕገ-ወጥ ፡ ሊሆን ፡ ቢችልም ፡ ሥራ ፡ ማቋረጦችን ፡ በቀጥታ ፡ የሚመለከት ፡ ምንም ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ቍጥር ፡ ያለ ፡ አይመስልም ። ለምሳሌ ፡ ከዚህ ፡ በታች ፡ በታተተው ፡ የኢ ፡ አ ፡ መ ፡ ጉዳይ ፡ ሥራ ፡ ያቋረጡት ፡ ሠራተኞች ፡ በፍርድ ፡ ቤት ፡ የተፈረደባቸው ፡ የወንጀ ለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ቍጥር ፡ ፫፻፶፱ንና ፡ የደንብ ፡ ተላላፊ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ቍጥር ፡ ፯፻፴፫ን ፡ ተላ ልፈዋል ፡ ተብሎ ፡ ነው ። ቃደሰ ፡ አብዲ ፡ ፖብሊክ ፡ ሰርቪስ ፡ ስትራይክስ ፡ ኢን ፡ ኢትዮጵያ ፡ (ያልታተመ ፡ ሕግ ፡ ፋኩልቲ ፡ ፲፱፻፶፱ ፡ ዓ ፡ ም ፡) ይመለከቷል ።

እንደ ፡ ከፍተኛ ፡ ደመወዝ ፡ የመሳሰሉትን ፡ ሌሎች ፡ ግቦች ፡ ለማግኘት ፡ ሲባል ፡ ብቻ ፡ ነው ። ስለ ፡ ሁለተኛው ፡ ሁኔታ ፡ ማለት ፡ ሥራ ፡ ማቋረጡ ፡ በሕግ ፡ በተከለ ከለበት ፡ ጊዜ ፡ ስለ ፡ አሠሪና ፡ ሠራተኞች ፡ ጉዳይ ፡ ከወጣው ፡ አዋጅ ፡ (አዋጁ ፡ በእነዚህ ፡ ጓዶች ፡ ላይ ፡ ተፈጻሚ ፡ አይደለም) ፡ እና ፡ በመንግሥት ፡ ሠራተኞች ፡ ላይ ፡ ብቻ ፡ ተፈጻሚ ፡ ከሆነው ፡ ልዩ ፡ ሕግ ፡ በስተቀር ፡ ይህን ፡ የመሰለ ፡ ሕግ ፡ በአሁኑ ፡ ጊዜ ፡ ያለ ፡ አይመስልም ።

በተጨማሪም ፡ ቍጥር ፡ ፪፻፲፻፷፭(፩) ፡ ተፈጻሚ ፡ በሚሆንበት ፡ ጊዜ ፡ እንኳን ፤ ሠራተኞችን ፡ ሥራ ፡ እንዳያቋርጡ ፡ አይከለክላቸውም ። በቍጥሩ ፡ ውስጥ ፡ በተ ዘረዘሩት ፡ ሁኔታዎች ፡ ሥራ ፡ የሚያቋርጡት ፡ ሠራተኞች ፡ የወንጀል ፡ ቅጣቶች ፡ ወይም ፡ ወደ ፡ ሥራ ፡ እንዲመለሱ ፡ የሚሰጥ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ትእዛዝ ፡ በቍ ጥሩ ፡ መሠረት ፡ [8] አይፈጸምባቸውም ። በሌላ ፡ ሁኔታ ፡ ሊሰጣቸው ፡ የሚገባቸ ውን ፡ የሥራ ፡ ስንብት ፡ ክፍያ ፡ ያጣሉ ፤ ደግሞም ፡ ሥራ ፡ ማቋረጡ ፡ የሥራውን ፡ ውል ፡ የሚያፈርሰው ፡ ከሆነ ፡ በአሠሪያቸው ፡ ላይ ፡ ላደረሱት ፡ ጉዳት ፡ ተጠያቂ ፡ ይሆናሉ ። [9]

በመንግሥት ፡ ሠራተኞች ፡ ዘንድ ፡ ሁኔታው ፡ ሌላ ፡ ነው ። በዚህና ፡ በሌላ ፡ ረገድ ፡ የመንግሥት ፡ ሠራተኞችን ፡ የሚመለከቱት ፡ ልዩ ፡ ሕጎች ፡ ሲሆኑ ፡ እነርሱም ፡ በ፲፱፻፶፬ ፡ ዓ ፡ ም ፡ የወጣው ፡ የመንግሥት ፡ ሠራተኞች ፡ ማስተዳደሪያ ፡ ጠቅላይ ፡ መሥሪያ ፡ ቤትና ፡ የመንግሥት ፡ ሠራተኞች ፡ ትእዛዝ ፡ እንዲሁም ፡ በት እዛዙ ፡ መሠረት ፡ በ፲፱፻፶፭ ፡ ዓ ፡ ም ፡ የወጡት ፡ ደንቦች ፡ ናቸው ። [10] የደንብቹ ፡ ቍጥር ፡ ፳፫ ፡ የመንግሥት ፡ ሠራተኞች ፡ በስምምነት ፡ ሥራን ፡ እንዳያቋርጡ ፡ ፈጽሞ ፡ ይከለክላል ። ይህ ፡ ክልከላ ፡ ትርፍ ፡ በሚያስገኙ ፡ የሥራ ፡ ድርጅቶች ፡ ውስጥ ፡ ለተቀጠሩ ፡ የመንግሥት ፡ ሠራተኞች ፡ ስለ ፡ አሠሪና ፡ ሠራተኛ ፡ ጉዳይ ፡ በወጣው ፡ አዋጅ ፡ ምናልባት ፡ በስውር ፡ ተሽሮ ፡ ይሆናል ። እነዚህ ፡ የመንግሥት ፡ ሠራተኞች ፡ አዋጁ ፡ ስለ ፡ ሠራተኛ ፡ ከሚሰጠው ፡ ትርጓሜ ፡ ውጭ ፡ አይደሉም ፤ ስለዚህም ፡ ለሠራተኛ ፡ ማኅበሮች ፡ በአዋጁ ፡ የተሠጣቸውን ፡ መብቶች ፡ ያላ ቸው ፡ ድርጅቶችን ፡ ሊያቋቁሙ ፡ ይችላሉ ፤ ይህም ፡ መብት ፡ ሥራ ፡ የማቋረጥን ፡

---

8. ሥራ ፡ ማቋረጡ ፡ በሕግ ፡ ሕገ-ወጥ ፡ ተብሎ ፡ ተደንግጐ ፡ ስለነበር ፡ ቍጥር ፡ ፪፻፲፻፷፭(፩) ፡ ተፈጻሚ ፡ ቢሆን ፡ ሕጉ ፡ የራሱን ፡ ፍትሐ ፡ ብሔራዊ ፡ ወይም ፡ ወንጀላዊ ፡ ውጤቶችን ፡ ሊያስከ ትል ፡ ይችላል ። ሆኖም ፡ ቍጥሩ ፡ ተፈጻሚ ፡ የሚሆነው ፡ ሥራ ፡ ማቋረጡ ፡ በሕዝብ ፡ ባለሥል ጣኖች ፡ ሕገ-ወጥ ፡ ተብሎ ፡ ስለነበር ፡ ከሆነ ፡ ምንም ፡ ፍትሐ ፡ ብሔራዊ ፡ ወይም ፡ ወንጀላዊ ፡ ውጤቶች ፡ (ቍጥር ፡ ፪፻፲፻፷፭(፩) ፡ ተፈጻሚ ፡ ከመሆኑ ፡ በስተቀር) ፡ ሊከተሉ ፡ የሚችሉ ፡ አይመ ስልም ፤ ሕገ-ወጥ ፡ የተባለው ፡ እነዚህ ፡ ውጤቶች ፡ እንዲከተሉ ፡ በሚያዝ ፡ ሥልጣን ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ ካልሆነ ፡ በስተቀር ። እንዲያውም ፡ የሕዝብ ፡ ባለሥልጣኑ ፡ በሌላ ፡ ሕግ ፡ ሥራ ፡ ማቋ ረጡ ፡ ሕገ-ወጥ ፡ ነው ፡ ለማለት ፡ ሥልጣን ፡ ካልተሰጠው ፡ በስተቀር ፡ ቍጥር ፡ ፪፻፲፻፷፭(፩) ፡ ራሱ ፡ ተፈጻሚ ፡ እንዲሆን ፡ ታስቦ ፡ ነበርን ፡ ብሎ ፡ ለመጠየቅ ፡ እንኳን ፡ ይቻላል ።

9. ስለ ፡ አሠሪና ፡ ሠራተኛ ፡ ጉዳይ ፡ በወጣው ፡ አዋጅ ፡ ለተመለከቱት ፡ ሠራተኞችም ፡ ቍጥር ፡ ፪፻፲፻፷፭ ፡ ተፈጻሚነት ፡ ያለው ፡ ይመስላል ፤ ለነሱም ፡ አዋጁ ፡ ሳይመለሰው ፡ ቢያንስ ፡ ለአንድ ፡ ዋና ፡ ጥያቄ ፡ ከፊል ፡ መልስ ፡ ይሰጣል ። ጥያቄውም ፡ ሥራ ፡ ያቋረጡ ፡ ሠራተኞች ፡ አሠሪው ፡ በሥራ ፡ ማቋረጡ ፡ ወቅት ፡ እነሱን ፡ ለመተካት ፡ ከቀጠራቸው ፡ ሠራተኞች ፡ ጋር ፡ ሲተያዩ ፡ መብታቸው ፡ ምንድር ፡ ነው? ቍጥር ፡ ፪፻፲፻፷፭(፪) ፡ አሠሪው ፡ ሥራ ፡ አቋራጮቹን ፡ ሥራ ፡ ማቋረጡ ፡ ሲያቆም ፡ እንደገና ፡ እንዲቀጥራቸው ፡ ወይም ፡ ያለ ፡ በቂ ፡ ምክንያት ፡ ሲሰናበቱ ፡ የሚገባቸውን ፡ ካሣ ፡ እንዲከፍላቸው ፡ የሚጠይቅ ፡ ይመስላል ።

10. የ፲፱፻፶፬ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ትእዛዝ ፡ ቍጥር ፡ ፳፫ ፡ ነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፡ ፳፩ኛ ፡ ዓመት ፡ ቍጥር ፡ ፫ና ፡ የ፲፱፻፶፭ ዓ ፡ ም ፡ የሕግ ፡ ክፍል ፡ ማስታወቂያ ፡ ቍጥር ፡ ፪፻፷፱ ፡ ነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፡ ፳፪ኛ ፡ ዓመት ፡ ቍ ጥር ፡ ፯ ። የሥራ ፡ ውሎችን ፡ የሚመለከቱት ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ቍጥሮች ፡ ለመንግሥት ፡ ሠራ ተኞች ፡ ተፈጻሚነት ፡ እንደሌላቸው ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቍጥር ፡ ፪፻፲፻፶፫ ፡ ተደንግጓል ።

መብት ፡ የሚጨምር ፡ ይመስላል ። [11] ሆኖም ፡ በአብዛኛዎቹ ፡ የመንግሥት ፡ ሠራተኞች ፡ ላይ ፡ ክልከላው ፡ የጸና ፡ ነው ።

## በሕዝብ ፡ አገልግሎቶች ፡ ውስጥ ፡ ያሉ ፡ ሠራተኞች ።

በሕዝብ ፡ አገልግሎት ፡ ውስጥ ፡ ያሉ ፡ የሠራተኞች ፡ ሥራ ፡ የማቋረጥ ፡ መብት ፡ ስለ ፡ አሠሪና ፡ ሠራተኛ ፡ ጉዳይ ፡ በወጣው ፡ አዋጅ ፡ በራሱ ፡ የተወሰነ ፡ ነው ። ወሳኙም ፡ ደንብ ፡ አንቀጽ ፡ ፪/ደ/፳(፪)(ሰ) ፡ ሲሆን ፡

"ጉዳዩ ፡ የሚመለከተው ፡ የሥራ ፡ ድርጅት ፡ ለሕዝብ ፡ የሚሰጠው ፡ አገልግሎት ፡ ለምሳሌ ፡ ያህል ፡ የኤሌክትሪክ ፡ የቴሌፎንና ፡ የቴሌግራፍ ፡ መገናኛዎች ፡ የትራንስፖርት ፡ አገልግሎት ፡ እጅግ ፡ አስፈላጊ ፡ በመሆናቸው ፡ ሥራውን ፡ በማቋረጥ ፡ በሕዝብ ፡ ላይ ፡ ብርቱ ፡ ጉዳት ፡ የሚያመጣ" ፡ በሆን ፡ ጊዜ ፡ በሠራተኞችም ፡ ሆነ ፡ በሠራተኛ ፡ ማኅበር ፡ የሚደረግ ፡ ሥራ ፡ ማቋረጥን ፡ "ተገቢ ፡ ያልሆነ ፡ የሥራ ፡ አፈጻጸም" ፡ ያደርገዋል ፤ ስለዚህም ፡ ሥራ ፡ ማቋረጡን ፡ ሕገ-ወጥ ፡ ያደርገዋል ። [12]

በአንድ ፡ በኩል ፡ የዚህ ፡ ደንብ ፡ ፍች ፡ ፈጽሞ ፡ ግልጽ ፡ ነው ። በዚህ ፡ ደንብ ፡ አነጋገር ፡ ውስጥ ፡ የሚገቡ ፡ ሥራ ፡ ማቋረጦች ፡ ሕገ-ወጥ ፡ ናቸው ፣ ደግሞም ፡ ሥራ ፡ ማቋረጡ ፡ በሥራው ፡ ድርጅት ፡ ወይም ፡ በሚሰጠው ፡ አገልግሎት ፡ ጠቃሚነት ፡ በሕዝብ ፡ ላይ ፡ ብርቱ ፡ ጉዳት ፡ የሚያመጣ ፡ ከሆነ ፡ ሥራ ፡ ማቋረጡ ፡ በደንቡ ፡ አነጋገር ፡ ውስጥ ፡ ይገባል ። ትርጉም ፡ የሚያሻው ፡ ዋናው ፡ ጥያቄ ፡ የተነሳው ፡ "በሕዝብ ፡ ላይ ፡ ብርቱ ፡ ጉዳት ፡ የሚያመጣ" ፡ የሚለውን ፡ ጭብጥ ፡ የሚመለከት ፡ ነው ። ወይም ፡ ይልቅስ ፡ ጥያቄው ፡ ይህ ፡ ጭብጥ ፡ በንዑስ ፡ አንቀጽ ፡ (ሰ) ፡ ስር ፡ አንድ ፡ ጉዳይ ፡ ለአሠሪና ፡ ሠራተኛ ፡ ጉዳይ ፡ ቦርድ ፡ ሲቀርብ ፡ ጭብጥ ፡ ነው ፡ ወይ ፡ የሚለው ፡ ጥያቄ ፡ ነበር ። ለዚህ ፡ ጥያቄ ፡ ሁለት ፡ መልሶች ፡ ተሰጥተዋል ።

<u>የመጀመሪያው ፡ አተረጓጐም</u> ፦ በደራሲው ፡ አስተያየት ፡ አንድ ፡ ሥራ ፡ ማቋረጥ ፡ ተገቢ ፡ ያልሆነ ፡ የሥራ ፡ አፈጻጸም ፡ ነው ፡ የሚል ፡ መደምደሚያ ፡ ለመስጠት ፡ <u>ቦርዱ ፡</u> ሁለት ፡ ፍሬ ፡ ነገሮችን ፡ እንዲያጣራ ፡ ያስፈልጋል ። (ቃሉ ፡ የተከመረበትን ፡ ምክንያት ፡ በቅርቡ ፡ እንገልጻለን) ፡ እነርሱም ፡ (፩) ፡ ሥራ ፡ ማቋረጡ ፡ በሕዝብ ፡ ላይ ፡ ብርቱ ፡ ጉዳት ፡ ሊያመጣ ፡ መቻሉንና ፡ ሊመጣ ፡ የሚችለውም ፡ ጉዳት ፡ ምክንያት ፡ "ጉዳዩ ፡ የሚመለከተው ፡ የሥራ ፡ ድርጅት ፡ ለሕዝብ ፡ የሚ

---

11\. አንቀጽ ፡ ሐያ ፡ (ሀ) ፡ የሠራተኛ ፡ ማኅበሮችን ፡ "ሕጋዊ ፡ ሥራዎችን ፡ ሁሉ ፡ ለመሥራት" ፡ ይፈቅድላቸዋል ። ይህ ፡ አንቀጽ ፡ የቀድሞውን ፡ የቁጥር ፡ ፹፫ን ፡ ክልከላ ፡ ስለ ፡ አሠሪና ፡ ሠራተኛ ፡ ጉዳይ ፡ ለወጣው ፡ አዋጅ ፡ አፈጻጸም ፡ ሠራተኞች ፡ ለሆኑት ፡ የመንግሥት ፡ ሠራተኞችም ፡ እንኳን ፡ እንዳለ ፡ (ተፈጻሚ ፡ እንዳይሆን) ፡ ይተዋል ፡ ተብሎ ፡ ለማንበብ ፡ ቢቻልም ፡ ቍጥሩ ፡ በራሱ ፡ በአዋጁ ፡ ከተከለከሉት ፡ ሁኔታዎች ፡ በስተቀር ፡ በሠራተኛ ፡ ማኅበር ፡ የሚደረጉ ፡ ሥራ ፡ ማቋረጦችን ፡ ይፈቅዳል ፡ ብሎ ፡ ማንበቡ ፡ የበለጠ ፡ ተገቢ ፡ ይመስላል ። ያም ፡ ሆነ ፡ ይህ ፡ ይህ ፡ ጭብጥ ፡ በይበልጥ ፡ ለምርምር ፡ ያህል ፡ የተነሳ ፡ ነው ፤ ምክንያቱም ፡ ትርፍ ፡ በሚያስገኙ ፡ የመንግሥት ፡ ድርጅቶች ፡ የሚሠሩ ፡ አብዛኛዎቹ ፡ የመንግሥት ፡ ሠራተኞች ፡ ከመንግሥት ፡ ሠራተኞች ፡ ክፍል ፡ ውጭ ፡ በመሆናቸው ፡ ከሕግ ፡ ክፍል ፡ ማስታወቂያ ፡ ቍጥር ፡ ፹፫ ፡ ሥልጣን ፡ ውጭ ፡ ተደርገዋል ። ለምሳሌ ፡ ያህል ፡ ለኢትዮጵያ ፡ አየር ፡ መንገድ ፡ ሠራተኞች ፡ ይህን ፡ የሚያደርገውን ፡ የ፲፱፻፷ ፡ ዓ ፡ ም ፡ የሕግ ፡ ክፍል ፡ ማስታወቂያ ፡ ቍጥር ፡ ፲፱፻፷፬ ፡ <u>ነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፡</u> ፳፫ኛ ፡ ዓመት ፡ ቍጥር ፡ ፲፪ን ፡ ይመለከቷል ።

12\. አንቀጽ ፡ ሐያ ፡ ስምንት ።

ሲጠው ፡ አገልግሎት ፡ . . . እጅግ ፡ አስፈላጊ ፡ በመሆናቸው” ፡ ነው ። ከጥቂቶች ፡ ሥራ ፡ ማቋረጦች ፡ ሌላ ፡ ማናቸውም ፡ ሥራ ፡ ማቋረጥ ፡ በሕዝብ ፡ ላይ ፡ ብርቱ ፡ ጉዳት ፡ ሊያደርስ ፡ የሚችለው ፡ በንዑስ ፡ አንቀጽ ፡ (ሰ) ፡ በተገለጹት ፡ ምክንያቶች ፡ ስለሆነ ፡ ሁለተኛውን ፡ ፍሬ ፡ ነገር ፡ ማጣራት ፡ ችግር ፡ የሚፈጥር ፡ አይመስልም ። በዚህ ፡ አተረጓጎም ፡ ስር ፡ ለቦርዱ ፡ ዋናው ፡ ጥያቄ ፡ ብርቱ ፡ የሕዝብ ፡ ጉዳት ፡ ሊመጣ ፡ ይችላልን ፡ የሚለው ፡ ነው ።

<u>ሁለተኛው ፡ አተረጓጎም</u> ፡— በቦርዱ ፡ ተቀባይነት ፡ ያገኘ ፡ የሚመስለው ፡ ሌላው ፡ አስተያየት ፡ በንዑስ ፡ አንቀጽ ፡ (ሰ) ፡ ውስጥ ፡ እንደ ፡ ማመላለሻ ፡ (ትራንስፖርት) ፡ በተለይ ፡ በተዘረዘሩት ፡ አገልግሎቶች ፡ ላይ ፡ የተመረኮዘ ፡ ነው ። በዚህ ፡ አስተያየት ፡ መዘርዘራቸው ፡ በነዚህ ፡ አገልግሎቶች ፡ ላይ ፡ የሚደረግ ፡ ሥራ ፡ ማቆም ፡ በሕዝብ ፡ ላይ ፡ ብርቱ ፡ ጉዳት ፡ ማምጣቱን ፡ <u>ምክር ፡ ቤቱ ፡ (ፓርላማው)</u> ፡ መወሰኑን ፡ ያመለክታል ። ስለዚህም ፡ በአንድ ፡ የተለየ ፡ ጉዳይ ፡ ውስጥ ፡ ያለ ፡ ሥራ ፡ ማቋረጥ ፡ በሕዝብ ፡ ላይ ፡ ብርቱ ፡ ጉዳት ፡ ያመጣ ፡ እንደሆን ፡ ቦርዱ ፡ መጠየቅ ፡ በጠቅላላው ፡ አያስፈልገውም ። ሥራ ፡ ማቋረጡ ፡ ከተዘረዘሩት ፡ አገልግሎቶች ፡ በአንዱ ፡ ላይ ፡ እተደረገ ፡ ድረስ—ደግሞም ፡ ከጥቂቶች ፡ በስተቀር ፡ በንዑስ ፡ አንቀጽ ፡ (ሰ) ፡ ስር ፡ የሚነሱት ፡ ጉዳዮች ፡ ይህን ፡ ዓይነት ፡ ሥራ ፡ ማቋረጥ ፡ የሚመለከቱ ፡ ናቸው ፤ ቦርዱ ፡ የምክር ፡ ቤቱን ፡ ውሳኔ ፡ ተመርኩዞ ፡ ጉዳዩን ፡ ሊወስን ፡ ይችላል ።

ምናልባት ፡ ማናቸውም ፡ አተረጓጎም ፡ ቢሆን ፡ የንዑስ ፡ አንቀጽ ፡ (ሰ)ን ፡ ቋንቋ ፡ ወይም ፡ ዓላማ ፡ በብርቱ ፡ አያዛንፈውም ፤ ደግሞም ፡ ሁለተኛው ፡ አተረጓጎም ፡ በአንዳንድ ፡ ጉዳዮች ፡ ላይ ፡ የተወሳሰበ ፡ የሚሆነውን ፡ ፍሬ ፡ ነገርን ፡ የማጣራት ፡ ተግባር ፡ በአብዛኛው ፡ ጉዳይ ፡ ላይ ፡ ባለማስፈለጉ ፡ ጠቃሚነት ፡ አለው። ሆኖም ፡ የመጀመሪያው ፡ አተረጓጎም ፡ ከአንቀጹ ፡ አነጋገር ፡ ጋር ፡ በይበልጥ ፡ የሚስማማ ፡ ይመስላል ።

ምናልባት ፡ ይህ ፡ አስተያየት ፡ የበለጠ ፡ ሊብራራ ፡ የሚችለው ፡ የንዑስ ፡ አንቀጽ ፡ (ሰ) ፡ ሐረጎች ፡ እንደሚከተለው ፡ እንደገና ፡ ቢሳኩና ፡ በሐረጉ ፡ የተጠቀሰውን ፡ የሥራ ፡ ማቋረጥ ፡ ቢያመለክቱ ፡ ነው ፡—

“በሕዝብ ፡ ላይ ፡ ብርቱ ፡ ጉዳት ፡ ሊያመጡ ፡ የሚችሉ ፡ ጉዳዩ ፡ የሚመለከተው ፡ የሥራ ፡ ድርጅት ፡ ለሕዝብ ፡ በጣም ፡ አስፈላጊ ፡ በመሆኑ ፡ ወይም ፡ የሚሰጡት ፡ አገልግሎቶች ፡ ዓይነት ፡ አስፈላጊ ፡ በመሆናቸው ፡ በሚከተሉት ፡ ሳይወሰን ፡ ለምሳሌ ፡ ያሀል ፡ የመብራት ፡ ኃይል ፡ ውሃና ፡ ሌሎችም ፡ የሕዝብ ፡ አገልግሎቶች ፡ የስልክና ፡ የቴሌግራፍ ፡ መገናኛዎችና ፡ የሕዝብ ፡ ማመላለሻ ፡ አገልግሎቶች” ። በዚህ ፡ አሰካክ ፡ መሠረት ፡ አንቀጹ ፡ “በሕዝብ ፡ ላይ ፡ ብርቱ ፡ ጉዳት ፡ ሊያመጡ ፡ የሚችሉ” ፡ ሥራ ፡ ማቋረጦችን ፡ በመጥቀስ ፡ ይጀመራል ። አንቀጹ ፡ እዚህ ፡ ላይ ፡ ቢያቆም ፡ ኖሮ ፡ ቦርዱ ፡ በያንዳንዱ ፡ ጉዳይ ፡ ላይ ፡ የዚህ ፡ ዓይነት ፡ ጉዳት ፡ ሊመጣ ፡ ስለመቻሉ ፡ መወሰን ፡ እንዳለበት ፡ አንቀጹ ፡ ስለ ፡ መጠየቁ ፡ ምንም ፡ ጥርጥር ፡ አይኖርም ። እንግዲያስ ፡ የተቀሩት ፡ የአንቀጹ ፡ ቃላት ፡ አስፈላጊነት ፡ ምንድር ፡ ነው? የተቀሩት ፡ ቃላት ፡ አንቀጹ ፡ የሚመለከታቸውን ፡ ሥራ ፡ ማቋረጦች ፡ በሕዝብ ፡ ላይ ፡ ብርቱ ፡ ጉዳት ፡ ሊያመጡ ፡ በሚችሉት ፡ የተለዩ ፡ ምክንያቶች ፡ የወሰኗቸው ፡ ይመስላል ። የተለዩት ፡ ምክንያቶችም ፡ ጉዳዩ ፡ የሚመለከተው ፡ የሥራ ፡ ድርጅት ፡ ለሕዝብ ፡ በጣም ፡ አስፈላጊ ፡ መሆኑ ፡ ወይም ፡ የሚሰጡት ፡ አገልግሎቶች ፡ ዓይነት ፡ አስፈላጊ ፡ መሆና

ቸው ፡ ናቸው ። የልዩ ፡ አገልግሎቶችም ፡ ዝርዝር ፡ የሚገኘው ፡ እላይ ፡ በተጠቀሰው ፡ ወሰን ፡ አገባብ ፡ ውስጥ ፡ ነው ። ዝርዝሩ ፡ የምክር ፡ ቤቱ ፡ (የፓርላማ) ፡ ውሳኔ ፡ ነው ፤ ውሳኔው ፡ ግን ፡ የሚደነግገው ፡ የተዘረዘሩት ፡ አገልግሎቶች ፡ "አስፈላጊ" ፡ መሆናቸውን ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ በነርሱ ፡ ላይ ፡ የተደረገ ፡ ማናቸውም ፡ ሥራ ፡ ማቋረጥ ፡ በሕዝብ ፡ ላይ ፡ ብርቱ ፡ ጉዳት ፡ ማምጣት ፡ መቻሉን ፡ አይደለም ።

በ"አስፈላጊ" ፡ አገልግሎት ፡ ላይ ፡ የሚደረግ ፡ ሥራ ፡ ማቋረጥ ፡ በሕዝብ ፡ ላይ ፡ ብርቱ ፡ ጉዳት ፡ ሊያመጣ ፡ የሚችል ፡ ይመስል ፡ ይሆናል ፤ አለበለዚያ ፡ አገልግሎቱ ፡ አስፈላጊ ፡ ነው ፡ ሊባል ፡ አይቻልም ። ሆኖም ፡ ነገሩ ፡ የግድ ፡ (ሁል ጊዜ) ፡ እንደዚህ ፡ አይደለም ። ለምሳሌ ፡ ያህል ፡ በብዙ ፡ ኩባንያዎች ፡ የሚሰጥ ፡ በአዲስ ፡ አበባና ፡ በጂማ ፡ መካከል ፡ ያለ ፡ የአውቶቡስ ፡ አገልግሎትን ፡ እንውሰድ ። የአሠሪና ፡ ሠራተኛ ፡ ጉዳይ ፡ ቦርድ ፡ በአንዱ ፡ ኩባንያ ፡ ላይ ፡ ስለተደረገ ፡ ሥራ ፡ ማቋረጥ ፡ ምን ፡ ማድረግ ፡ አለበት? ሁለተኛውን ፡ አተረጓጎም ፡ ከተቀበልን ፡ መልሱ ፡ ግልጽ ፡ ነው ። በዚህ ፡ አተረጓጎም ፡ መሠረት ፡ ምክር ፡ ቤቱ ፡ በማመላለሻ ፡ ላይ ፡ የሚደረግ ፡ ሥራ ፡ ማቋረጥ ፡ ከተዘረዘሩት ፡ አገልግሎቶች ፡ አንዱ ፡ እንደመሆኑ ፡ መጠን ፡ በሕዝብ ፡ ላይ ፡ ብርቱ ፡ ጉዳት ፡ ለማምጣት ፡ መቻሉን ፡ ወስኗል ። ሥራው ፡ የተቋረጠበት ፡ ኩባንያ ፡ ማመላለሻን ፡ ይሰጣል ። ስለዚህ ፡ ሥራ ፡ ማቋረጡ ፡ በንዑስ ፡ አንቀጽ ፡ (ሰ) ፡ ስር ፡ ሕገ-ወጥ ፡ ነው ። ሆኖም ፡ ምክር ፡ ቤቱ ፡ የወሰነው ፡ ማመላለሻ ፡ አስፈላጊ ፡ አገልግሎት ፡ መሆኑን ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ በሕዝብ ፡ ላይ ፡ ብርቱ ፡ ጉዳት ፡ ሊያመጣ ፡ ይችላልን ፡ የሚለውን ፡ ጥያቄ ፡ ለቦርዱ ፡ ትቶለታል ፡ ካልን ፡ የነገሩ ፡ ሁኔታ ፡ ይለወጣል ። በአዲስ ፡ አበባና ፡ በአንድ ፡ የጠቅላይ ፡ ግዛት ፡ ታላቅ ፡ ከተማ ፡ መካከል ፡ ያለ ፡ ማመላለሻ ፡ ያለ ፡ ምክር ፡ ቤቱ ፡ ውሳኔ ፡ እንደ ፡ አስፈላጊ ፡ አገልግሎት ፡ እንደሚቆጠር ፡ አያጠራጥርም ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ይህን ፡ አገልግሎት ፡ በከፊል ፡ የሚያቆም ፡ ሥራ ፡ ማቋረጥ ፡ በሕዝብ ፡ ላይ ፡ ብርቱ ፡ ጉዳት ፡ ሊያመጣም ፡ ላያመጣም ፡ ይችላል ። እላይ ፡ ለምሳሌ ፡ በቀረበው ፡ ጉዳይ ፡ በሕዝብ ፡ ላይ ፡ ብርቱ ፡ ጉዳት ፡ ሊያመጣ ፡ መቻሉን ፡ ለመወሰን ፡ በአዲስ ፡ አበባና ፡ በጂማ ፡ መካከል ፡ በአውቶቡስ ፡ የሚንቀሳቀሰውን ፡ የሰውና ፡ የዕቃ ፡ ልክ ፡ በሥራ ፡ ማቋረጥ ፡ የተስፈራራው ፡ ኩባንያ ፡ የሚያመላልሰው ፡ የሰውና ፡ የዕቃ ፡ ድርሻ ፡ እንዲሁም ፡ ይህ ፡ ኩባንያ ፡ አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ የሚያጓጉዘውን ፡ ሰውና ፡ ዕቃ ፡ ሌሎቹ ፡ ኩባንያዎች ፡ ለመጫን ፡ ያላቸውን ፡ ችሎታ ፡ መመርመር ፡ ያስፈልጋል ።

ምንም ፡ እንኳን ፡ የአሠሪና ፡ ሠራተኛ ፡ ጉዳይ ፡ ቦርድ ፡ በነዚህ ፡ ሁለት ፡ ተንጻጻሪ ፡ አተረጓጎሞች ፡ መካከል ፡ ያለው ፡ አስተያየት ፡ እስካሁን ፡ ድረስ ፡ ፍጹም ፡ ግልጽ ፡ ባይሆንም ፡ (የዚህ ፡ ምክንያት ፡ በከፊል ፡ እንደ ፡ አዲስ ፡ አበባ—ጅማ ፡ አውቶቡስ ፡ ጉዳይ ፡ ላይ ፡ አጠራጣሪ ፡ ነገር ፡ መወሰን ፡ ስላልነበረበት ፡ ነው) ፡ ቦርዱ ፡ ሁለተኛውን ፡ አተረጓጎም ፡ የተቀበለ ፡ ይመስላል ። እስካሁን ፡ ድረስ ፡ ንዑስ ፡ አንቀጽ ፡ (ሰ)ን ፡ የሚመለከቱ ፡ ሁለት ፡ ጉዳዮች ፡ በቦርዱ ፡ ፊት ፡ ቀርበዋል ፡ የኢትዮጵያ ፡ አየር ፡ መንገድ ፡ ከሳሽ ፤ የኢትዮጵያ ፡ አየር ፡ መንገድ ፡ ሠራተኞች ፡ ማኅበር ፡ ተከሳሽ ፡ (የኢ ፡ አ ፡ መ ፡ ጉዳይ) ፡ እና ፡ የኢትዮጵያ ፡ ማመላለሻ ፡ አክሲዮን ፡ ማኅበር ፡ ከሳሽ ፤ የኢትዮጵያ ፡ ማመላለሻ ፡ አክሲዮን ፡ ማኅበር ፡ ሠራተኞች ፡ ማኅበር ፡ ተከሳሽ ፡ (የማመላለሻ ፡ ጉዳይ) ። [13] በጥቅምት ፡ ፲ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፹፯ ፡ ዓ፡

13. የሁለቱ ፡ ጉዳዮች ፡ ሐተታ ፡ የተወሰደው ፡ በግርጌ ፡ ማስታወሻ ፡ ፲ ፡ ከተጠቀሰው ፡ የታደሰ ፡ አብዲ ፡ ጽሑፍ ፡ ነው ።

ም ፡ የኢ ፡ አ ፡ መ ፡ ሠራተኞች ፡ ሥራ ፡ በማቋረጥ ፡ ዓለም ፡ አቀፉን ፡ አገልግሎት ፡ ሳይሆን ፡ ብሔራዊውን ፡ አገልግሎት ፡ አቋረጡ ። በዚያኑ ፡ ዕለት ፡ የአሠሪና ፡ የሠራተኞች ፡ ጉዳይ ፡ ቦርድ ፡ አስቸኳይ ፡ ስብሰባ ፡ አድርጐ ፡ የሚከተለውን ፡ ውሳኔ ፡ ሰጠ ።

"የኢ ፡ አ ፡ መ ፡ ሠራተኞች ፡ አቤቱታቸውን ፡ ስለ ፡ አሠሪና ፡ ሠራተኛ ፡ ጉዳይ ፡ በወጣው ፡ አዋጅ ፡ ፪፻፲/፲፱፻፷፫ ፡ መሠረት ፡ ለቦርዱ ፡ ስላላቀረቡ ፡ የኢ ፡ አ ፡ መ ፡ ሥራ ፡ የሕዝብ ፡ ማመላለሻ ፡ አገልግሎት ፡ ስለሆነ ፡ የዚህን ፡ ዓይነት ፡ ሥራ ፡ ማቆም ፡ በሕዝብ ፡ ላይ ፡ ብርቱ ፡ ጉዳት ፡ የሚያመጣ ፡ ስለሆነና ፡ በአንቀጽ ፡ ፴ (ደ) (፩) (፪) (ሰ) ፡ ስር ፡ የኢ ፡ አ ፡ መ ፡ ሠራተኞች ፡ በማናቸውም ፡ ሁኔታ ፡ ቢሆን ፡ ሥራ ፡ የማቋረጥ ፡ መብት ፡ ስለሌላቸው ፡ ቦርዱ ፡ እንደሚከተለው ፡ ያዝዛል ።

፭ በአንቀጽ ፡ ፲፪ (ሀ) (፪) በተሰጠው ፡ ሥልጣን ፡ መሠረት ፡ የኢ ፡ አ ፡ መ ፡ ሠራተኞች ፡ ሥራ ፡ ማቋረጡን ፡ አቁመው ፡ ወደ ፡ ሥራቸው ፡ ይመለሱ"

የሕዝብ ፡ ማመላለሻ ፡ ጉዳይ ፡ ከአንድ ፡ ዓመት ፡ ይበልጥ ፡ በኋላ ፡ ተነሳ ። የሕዝብ ፡ ማመላለሻ ፡ ኩባንያ ፡ በአዲስ ፡ አበባ ፡ ውስጥ ፡ የአውቶቡስ ፡ አገልግሎትን ፡ ያካሄዳል ። በታኅሣሥ ፡ ፲፱፻፷፭ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ሠራተኞቹ ፡ ለሁለት ፡ ቀናት ፡ ሥራ ፡ አቋረጡ ። በአዲስ ፡ አበባ ፡ የአውቶቡስ ፡ አገልግሎት ፡ ቆመ ። ከጥቂት ፡ ወራት ፡ በኋላ ፡ ቦርዱ ፡ በውሳኔው ፡ ላይ ፡

"አቤቱታውን ፡ ያቀረበው ፡ ኩባንያ ፡ ሰዎችን ፡ በኢትዮጵያ ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛቶችና ፡ በዋናው ፡ ከተማ ፡ በሙሉ ፡ ያመላልሳል ፤ ሥራው ፡ የማመላለሻ ፡ አገልግሎትን ፡ መስጠት ፡ ነው ። በማመላለሻ ፡ አገልግሎት ፡ የሚሠሩ ፡ ሠራተኞች ፡ በአንቀጽ ፡ ፴ (ደ) (፩) (፪) (ሰ) ፡ ሥራ ፡ ከማቋረጥ ፡ ተከልክለዋል"

ብሎ ፡ በየነ ።

የኢ ፡ አ ፡ መ ፡ ን ፡ ጉዳይ ፡ እንደቀደምት ፡ ብይን ፡ በመጥቀስ ፡ ቦርዱ ፡ ሠራተኞቹ ፡ ተገቢ ፡ ያልሆነ ፡ የሥራ ፡ አፈጻጸም ፡ በማድረግ ፡ ጥፋተኞች ፡ ናቸው ፡ አለ ።

<u>የኢ ፡ አ ፡ መ ፡ ጉዳይ</u> ፡ ለብቻው ፡ ሲወሰድ ፡ ስለ ፡ ንዑስ ፡ አንቀጽ ፡ (ሰ) ፡ አተረጓጐም ፡ ቦርዱ ፡ ስላለው ፡ አስተያየት ፡ የተጻረሩ ፡ (የተቃረኑ) ፡ ፍንጮች ፡ ይሰጣል ። ቦርዱ ፡ ሥራ ፡ ማቋረጡ ፡ በሕዝብ ፡ ላይ ፡ ብርቱ ፡ ጉዳት ፡ ለማምጣት ፡ መቻሉን ፡ በግልጽ ፡ ወሰነ ፤ ይህም ፡ የመጀመሪያውን ፡ አተረጓጐም ፡ መቀበሉን ፡ ያመለክታል ። በሌላው ፡ በኩል ፡ የኢ ፡ አ ፡ መ ፡ ሠራተኞች ፡ "በማናቸውም ፡ ሁኔታ ፡ ቢሆን ፡ ሥራ ፡ ለማቋረጥ ፡ መብት" ፡ የላቸውም ፡ የሚለው ፡ ውሳኔው ፡ የኢ ፡ አ ፡ መን ፡ የወሰድን ፡ እንደሆን ፡ በእያንዳንዱ ፡ ጉዳይ ፡ ላይ ፡ በሕዝብ ፡ ላይ ፡ ጉዳት ፡ ሊደርስ ፡ መቻሉን ፡ መመልከት ፡ አለማስፈለጉን ፡ ስለሚያመለክት ፡ ከመጀመሪያው ፡ አተረጓጐም ፡ የተለየ ፡ ይሆናል ።

ቦርዱ ፡ ምናልባት ፡ ሁለተኛውን ፡ አተረጓጐም ፡ ተቀብሏል ፡ ብለን ፡ ለመወሰን ፡ <u>የሕዝብ ፡ ማመላለሻን ፡ ጉዳይ</u> ፡ መመርኮዝ ፡ አለብን ። በመጀመሪያ ፡ <u>በኢ ፡ አ ፡ መ ፡ ጉዳይ</u> ፡ እንደወሰነው ፡ ሳይሆን ፡ <u>በሕዝብ ፡ ማመላለሻ ፡ ጉዳይ</u> ፡ ቦርዱ ፡ ሥራ ፡ ማቋረጡ ፡ በሕዝብ ፡ ላይ ፡ ብርቱ ፡ ጉዳት ፡ ማምጣቱን ፡ በግልጽ ፡ አልወሰነም ። ሁለተኛ ፡ ቦርዱ ፡ ክልከላውን ፡ የገለጸው ፡ ምንም ፡ የተለዩ ፡ ሁኔ

ታዎች ፡ እንደሌለው ፡ አድርጎ ፡ ሲሆን ፡ ውሳኔው ፡ እሬቱ ፡ ቀርቦ ፡ በነበረው ፡
ጉዳይ ፡ ለተመለከተው ፡ አንዱን ፡ ኩባንያ ፡ በመጥቀስ ፡ አልተወሰነም ። ውሳኔው ፡
የሚለው ፡ "በማመላለሻ ፡ አገልግሎት ፡ የሚሠሩ ፡ ሠራተኞች ፡ ከሥራ ፡ ማቋረጥ ፡
ተከልክለዋል ፡ . . . " ነው ። ይህ ፡ የውሳኔው ፡ ቃል ፡ እንዲሁ ፡ (ለብቻው) ፡ ሲነ
በብ ፡ በሚሰጠው ፡ ስሜት ፡ ሊወሰድ ፡ ከተቻለ ፡ የንዑስ ፡ አንቀጽ ፡ (ሰ)ን ፡ ሁለተ
ኛውን ፡ አተረጓጐም ፡ ቦርዱ ፡ ሙሉ ፡ በሙሉ ፡ የተቀበለው ፡ መሆኑን ፡ ያሳያል ።

ሆኖም ፡ የውሳኔው ፡ ቃል ፡ ለብቻው ፡ ሲነበብ ፡ በሚሰጠው ፡ ስሜት ፡ ለመ
ውሰድ ፡ ይቻላል ፡ ብሎ ፡ ከማመን ፡ በፊት ፡ ቃሉ ፡ በምን ፡ አገባብ ፡ እንደ ፡ ተነ
ገረ ፡ ማስታወሱ ፡ መልካም ፡ ነው ። የሕዝብ ፡ ማመላለሻ ፡ ጉዳይ ፡ እንደ ፡ የኢ ፡ አ ፡
መ ፡ ጉዳይ ፡ የተመለከተው ፡ በአንድ ፡ ዓይነት ፡ ማመላለሻ ፡ ሞኖፖሊ ፡ ያለው ፡
ኩባንያ ፡ ላይ ፡ የተደረገን ፡ ሥራ ፡ ማቋረጥ ፡ ነው ። በሕዝብ ፡ ማመላለሻ ፡ ኩባ
ንያ ፡ ላይ ፡ የተደረገ ፡ የተሳካ ፡ ሥራ ፡ ማቋረጥ ፡ የአዲስ ፡ አበባ ፡ ነዋሪዎችን ፡ ከታ
ክሲዎች ፡ በስተቀር ፡ ሌላ ፡ የሕዝብ ፡ ማመላለሻ ፡ ያሳጣቸዋል ፡ ባለፈውም ፡ ሥራ ፡
ማቋረጥ ፡ ጊዜ ፡ አሳጥቷቸዋል ። ታክሲዎቹም ፡ በሕዝብ ፡ ማመላለሻ ፡ አውቶቡ
ሶች ፡ የሚጓጓዙትን ፡ ለመጫን ፡ በቂ ፡ አይሆኑ ፡ ይሆናል ፡ በቂ ፡ ቢሆኑም ፡ ከአው
ቶቡሶቹ ፡ የበለጠ ፡ ውድ ፡ ናቸው ። ይህን ፡ በመሰለ ፡ ሁኔታ ፡ በሕዝብ ፡ ላይ ፡ ጉዳት
የሚያመጣ ፡ ነው ፡ አይደለም ፡ ብሎ ፡ መጠየቅ ፡ በመጀመሪያው ፡ አተረጓጐም ፡
እንኳን ፡ ምናልባት ፡ አስፈላጊ ፡ አይሆንም ። በሕዝብ ፡ ላይ ፡ ብርቱ ፡ ጉዳት ፡ የሚ
ያመጣ ፡ ነው ፡ አይደለም ፡ የሚለው ፡ ጥያቄ ፡ ይበልጥ ፡ አጠራጣሪ ፡ የሆነበት ፡
ጉዳይ ፡ እስኪገጥመው ፡ ድረስ ፡ ቦርዱ ፡ ሁለተኛውን ፡ አተረጓጐም ፡ ተቀብሏል ፡
ብሎ ፡ ማመን ፡ አይገባም ።

## የገደቡ ፡ ፍች ።

የመንግሥት ፡ ሠራተኞችና ፡ የሕዝብ ፡ አገልግሎት ፡ ሠራተኞች ፡ በሥራ ፡
ማቋረጥ ፡ መብት ፡ ረገድ ፡ አቋማቸው ፡ ተመሳሳይ ፡ ነው ። በምንም ፡ ሁኔታ ፡
ቢሆን ፡ የመንግሥት ፡ ሠራተኞች ፡ ሥራ ፡ ሊያቋርጡ ፡ አይችሉም ። የሕዝብ ፡ አገ
ልግሎት ፡ ሠራተኞችም ፡ በንዑስ ፡ አንቀጽ ፡ (ሰ) ፡ ሁለተኛ ፡ አተረጓጐም ፡ መሠ
ረት ፡ ሥራ ፡ ሊያቋርጡ ፡ አይችሉም ፤ በመጀመሪያውም ፡ አተረጓጐም ፡ እንኳን ፡
በብዙ ፡ ምናልባትም ፡ በአብዛኛዎቹ ፡ ሁኔታዎች ፡ ሥራ ፡ ከማቋረጥ ፡ ይከለከላሉ ።
ሆኖም ፡ የገደቡ ፡ ፍች ፡ ለሁለቱም ፡ ዓይነት ፡ ሠራተኞች ፡ አንድ ፡ አይደለም ።
ንዑስ ፡ አንቀጽ ፡ (ሰ) ፡ ሥራ ፡ ማቋረጥን ፡ በፍጹም ፡ ይከለክላል ፤ እንዲሁም ፡
በሕዝብ ፡ አገልግሎት ፡ ሠራተኞች ፡ አቋምና ፡ በተራ ፡ ሠራተኞች ፡ አቋም ፡ መካ
ከል ፡ ያለው ፡ ልዩነት ፡ በጣም ፡ የተቀነሰ ፡ ነው ፡ ብለን ፡ ብንወስድም ፡ የሕዝብ ፡
አገልግሎት ፡ ሠራተኞች ፡ ከአሠሪዎቻቸው ፡ ጋር ፡ ለመከራከር ፡ በሕግ ፡ ፊት ፡
ያላቸው ፡ አቋም ፡ የመንግሥት ፡ ሠራተኞች ፡ ካላቸው ፡ አቋም ፡ በይበልጥ ፡ የጠ
ነከረ ፡ ነው ፤ የሕዝብ ፡ አገልግሎት ፡ ሠራተኞች ፡ ሥራ ፡ እንዳያቋርጡ ፡ ምናል
ባት ፡ ፈጽሞ ፡ ቢከለከሉም ፡ ከዚህ ፡ ሌላ ፡ ስለ ፡ አሠሪና ፡ ሠራተኛ ፡ ጉዳይ ፡ በወ
ጣው ፡ አዋጅ ፡ ለሠራተኞች ፡ በተሰጡት ፡ መብቶች ፡ ለመጠቀም ፡ ነፃ ፡ ናቸው ።
ተሰብስበው ፡ የሠራተኛ ፡ ማኅበር ፡ ለማቋቋም ፡ ይችላሉ ፤ የሕዝብ ፡ አገልግሎት ፡
ሠራተኞች ፡ ማኅበር ፡ በሥራው ፡ ውስጥ ፡ ካሉት ፡ አብዛኞቹውን ፡ ሠራተኞች ፡

ከጨመረ ፡ አሠሪው ፡ ከሠራተኛው ፡ ማኅበር ፡ ጋር ፡ የኅብረት ፡ ክርክር ፡ ለማድረግ ፡ የሕግ ፡ ግዴታ ፡ ሳይኖርበት ፡ አይቀርም ።[14]

እንዚሁ ፡ መብቶች ፡ ራሳቸው ፡ (ለብቻቸው) ፡ ጠቃሚ ፡ ናቸው ። የአሠሪና ፡ ሠራተኛ ፡ ጉዳይ ፡ ቦርድ ፡ በተሰጠው ፡ ሰፊ ፡ ሥልጣን ፡ ምክንያት ፡ ጠቃሚነታቸው ፡ የላቀ ፡ ይሆናል ። የቦርዱ ፡ ተግባር ፡ በመሠረቱ ፡ ዳኝነት ፡ ነክ ፡ የሆነው ፡ ሕጋዊ ፡ መብቶችንና ፡ ግዴታዎችን ፡ መዳኘት ፡ ነው ። ተገቢ ፡ ያልሆነ ፡ የሥራ ፡ አፈጻጸም ፡ ተደርጓል ፡ ብሎ ፡ የሚቀርብን ፡ አቤቱታ ፡ ለመመርመር ፡ ያለው ፡ ሥልጣን ፡[15] ስለ ፡ አሠሪና ፡ ሠራተኛ ፡ ጉዳይ ፡ የወጣው ፡ አዋጅ ፡[16] የደነገገውን ፡ ግዴታዎች ፡ የማስፈጸም ፡ ሥልጣን ፡ ነው ፤ ዳግም ፡ በአሠሪና ፡ በሠራተኛ ፡ መካከል ፡ ያለውን ፡ የሥራ ፡ ክርክር ፡ ለመገላገል ፡ ያለው ፡ ሥልጣን ፡[17] አሠሪዎችና ፡ ሠራተኞች ፡ በኅብረት ፡ ስምምነታቸው ፡ የወሰኑትን ፡ ግዴታዎች ፡ የማስፈጸም ፡ ሥልጣን ፡ የሚጨምር ፡ ይመስላል ።[18] ሆኖም ፡ አዋጁ ፡ ውስጥ ፡ የሥራ ፡ ክርክሮች ፡ ሰፊ ፡ ትርጓሜ ፡ የተሰጣቸው ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ቦርዱ ፡ በእንዲህ ፡ ዓይነት ፡ ክርክሮች ፡ ላይ ፡ ያለው ፡ ሥልጣን ፡ የኅብረት ፡ ክርክሮችንም ፡ ማለት ፡ በአንድ ፡ በቀረበ ፡ ስምምነት ፡ ውስጥ ፡ የወገኖቹ ፡ መብቶችና ፡ ግዴታዎች ፡ ምን ፡ እንደሚሆኑ ፡ የሚነሱ ፡ ክርክሮችን ፡ ለመወሰን ፡ ያስችለዋል ።

ቦርዱ ፡ የኅብረት ፡ ክርክሮችን ፡ ለመገላገል ፡ ያለው ፡ ሥልጣን ፡ ቢያንስ ፡ ለሥራ ፡ ማቋረጥ ፡ መብት ፡ በከፊል ፡ ምትክ ፡ ሊሆን ፡ የሚችል ፡ ነው ። የሕዝብ ፡ አገልግሎት ፡ ሠራተኞች ፡ ማኅበር ፡ ግፋ ፡ ቢል ፡ ከተወሰኑ ፡ ሁኔታዎች ፡ በስተቀር ፡ ከአሠሪው ፡ ጥቅም ፡ ለማግኘት ፡ ሲባል ፡ በሕጋዊ ፡ መንገድ ፡ ሥራ ፡ ለማቋረጥ ፡

---

14. "ያለ ፡ ሥጋት ፡ (ለ) ፡ መነጋገር"ና ፡ "በተቻለ ፡ መጠን ፡ የሥራ ፡ ክርክሮችን ፡ በሰላማዊ ፡ መንገድ ፡ እንዲወሰኑ" ፡ ግዴታ ፡ ከሚደነግጉት ፡ ከንዑስ ፡ አንቀጾች ፡ ሐ ፡ ሁለት ፡ (ለ)ና ፡ (መ) ፡ ይህ ፡ ግዴታ ፡ ምናልባት ፡ ሊወሰድ ፡ ይቻል ፡ ይሆናል ። ሆኖም ፡ ንጥቡ ፡ ከአከራካሪነት ፡ አልወጣም ፤ ምክንያቱም ፡ እንዚህ ፡ ደንቦች ፡ የሚጠቅሱት ፡ የሠራተኛ ፡ ማኅበሮችንና ፡ የአሠሪዎች ፡ ማኅበሮችን ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ የግል ፡ አሠሪዎችን ፡ አይደለም ። ግዴታው ፡ የኅብረት ፡ ክርክር ፡ ከጀመሩ ፡ በኋላ ፡ አሠሪና ፡ ሠራተኞች ፡ ያለባቸውን ፡ ግዴታዎች ፡ በሚዘረዝሩት ፡ በቍጥር ፡ ፳፮ና ፡ ፳፯ ፡ ላይ ፡ በቀጥታ ፡ ሊመሠረት ፡ አለመቻሉን ፡ ማስታወስ ፡ ይገባል ። እዚህ ፡ ላይ ፡ ያለው ፡ ጥያቄ ፡ ይህን ፡ የኅብረት ፡ ክርክር ፡ ማድረግ ፡ አለባቸውን ፡ የሚለው ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ክርክሩን ፡ ሲያደርጉ ፡ ምን ፡ ዓይነት ፡ ምግባር ፡ ማሳየት ፡ አለባቸው ፡ የሚለው ፡ አይደለም ።

15. አንቀጽ ፡ አሥራ ፡ ሁለት ፡ ሀ) ፡ (፪) ።

16. ስለ ፡ አሠሪና ፡ ሠራተኛ ፡ ጉዳይ ፡ የወጣው ፡ አዋጅ ፡ የደነገጋቸውን ፡ ማናቸውንም ፡ ግዴታዎች ፡ በመጣስ ፡ በሠራተኛ ፡ ማኅበር ፡ በአሠሪ ፡ ወይም ፡ በአሠሪዎች ፡ ማኅበር ፡ የሚደረግ ፡ አድራጐት ፡ ተገቢ ፡ ያልሆነ ፡ የሥራ ፡ አፈጻጸም ፡ ነው ። አንቀጽ ፡ ሁለት ፡ ድ(፩)ና ፡ ድ (፪)(፩) ።

17. አንቀጽ ፡ ዐሥራ ፡ ሁለት ፡ ሀ) (፩) ።

18. አንቀጽ ፡ ዐሥራ ፡ ሁለት ፡ ሀ)(፩) ፡ የታሰበው ፡ ቦርዱ ፡ የሥራ ፡ ክርክሮችን ፡ በሚነካ ፡ ነገር ፡ ብቻ ፡ እንጂ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ በተመሠረቱ ፡ የውል ፡ ድርድሮች ፡ ላይ ፡ በሚነሳው ፡ አለመግባባት ፡ ተከራካሪዎችን ፡ ለመገላገል ፡ አይደለም ፡ ተብሏል ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ለዚህ ፡ ወሰን ፡ ከአዋጁ ፡ መሠረት ፡ ማግኘት ፡ በጣም ፡ ከባድ ፡ ነው ። እንዲያውም ፡ በአዋጁ ፡ መሠረት ፡ ቦርዱ ፡ የግል ፡ ውሎችን ፡ ትርጓሜ ፡ የሚነካ ፡ ክርክር ፡ ለማየት ፡ የሚችል ፡ ይመስላል ፡ (ከአንቀጽ ፡ ፴፫ ፡ ተቃራኒውን ፡ መውሰድ ፡ ከል ቻልን) ። በአሠሪና ፡ ሠራተኛ ፡ መካከል ፡ ባለው ፡ ግንኙነት ፡ በሙሉ ፡ የሚከተሉትን ፡ መወሰን ፡ ሊያስፈልግ ፡ ነው ፡ (፩) ፡ የአሠሪና ፡ ሠራተኛ ፡ ጉዳይ ፡ ቦርዱ ፡ በምን ፡ ሁኔታ ፡ ለብቻው ፡ (ማንም ፡ የማይጋራው) ፡ ሥልጣን ፡ እንዳለው ፡ (፪) ፡ ቦርዱና ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ በምን ፡ ሁኔታዎች ፡ ሁለቱም ፡ ሥልጣን ፡ እንዳላቸው ፡ (፫) ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ በምን ፡ ሁኔታ ፡ ማንም ፡ የማይጋራቸው ፡ ሥልጣን ፡ እንዳላቸው ። የሥራ ፡ ክርክርን ፡ በሚነካ ፡ ነገር ፡ ተከራካሪዎችን ፡ ከመገላገል ፡ ውጭ ፡ በሆነ ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶችና ፡ ቦርዱ ፡ ሁለቱም ፡ ሥልጣን ፡ ያላቸው ፡ ይመስላል ። የሥራ ፡ ክርክሮች ፡ አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ መብቶችን ፡ በመዳኘት ፡ ሊወሰኑ ፡ አይችሉም ፤ ስለዚህ ፡ ለፍርድ ፡ ቤቶች ፡ የሚገቡ ፡ ጉዳዮች ፡ አይደሉም ።

አሠሪውን ፡ ሊያስፈራራ ፡ አይችልም ። ነገር ፡ ግን ፡ በማናቸውም ፡ ሁኔታ ፡ ክርክሩን ፡ ለአሠሪና ፡ ሠራተኛ ፡ ጉዳይ ፡ ቦርድ ፡ ሊያቀርብ ፡ ይችላል ። ክርክሩን ፡ ለቦርዱ ፡ ለማቅረብ ፡ በማስፈራራት ፡ ወይንም ፡ ለቦርዱ ፡ በማቅረብ ፡ የሠራተኛው ፡ ማኅበር ፡ በንትርክና ፡ ለአሠሪው ፡ የትክክለኛነት ፡ ስሜት ፡ በማመልከት ፡ ከሚያገኘው ፡ ጥቅም ፡ ይበልጥ ፡ ለማግኘት ፡ ተስፋ ፡ አለው ።

የዳበረ ፡ የሠራተኛ ፡ ማኅበር ፡ ወደ ፡ ቦርዱ ፡ የመሄድን ፡ መብት ፡ ላልተወሰነ ፡ ሥራ ፡ የማቋረጥ ፡ መብት ፡ አጥጋቢ ፡ ምትክ ፡ አድርጎ ፡ ላይቆርጠው ፡ ይቻላል ። ሆኖም ፡ በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ ማናቸውም ፡ የሠራተኛ ፡ ማኅበር ፡ ያልተወሰነ ፡ ሥራ ፡ የማቋረጥ ፡ መብት ፡ እንደ ፡ ሌለው ፡ መታወስ ፡ አለበት ። [19] ሥራ ፡ የማቋረጥ ፡ መብት ፡ የበዙ ፡ ገደቦች ፡ አሉበት ፤ ከነዚሁም ፡ ዋነኛው ፡ የሠራተኛ ፡ ማኅበር ፡ ሥራ ፡ ከማቋረጡ ፡ ቢያንስ ፡ ከስድሳ ፡ ቀናት ፡ በፊት ፡ የሥራውን ፡ ክርክር ፡ ለቦርዱ ፡ እንዲያቀርብ ፡ የሚጠይቀው ፡ የስድሳ ፡ ቀኑ ፡ ደንብ ፡ መሆኑ ፡ ተረጋግጧል ። ደንቡም ፡ የሠራተኛው ፡ ማኅበር ፡ የጠየቀውን ፡ ለማግኘት ፡ ሥራ ፡ ለማቋረጥ ፡ ከመቻሉ ፡ በፊት ፡ የአሠሪና ፡ ሠራተኛ ፡ ጉዳይ ፡ ቦርድ ፡ ተከራካሪዎቹን ፡ የመገላገል ፡ ዕድል ፡ ይሰጠዋል ፤ ቦርዱም ፡ ክርክሩን ፡ በስድሳው ፡ ቀን ፡ ውስጥ ፡ ከገላገለ ፤ [20] ከዚያ ፡ በኋላ ፡ የሠራተኛው ፡ ማኅበር ፡ ሥራ ፡ ማቋረጥ ፡ አይችልም ፤ ምክንያቱም ፡ ሥራ ፡ ማቋረጡ ፡ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ የቦርዱን ፡ የግልግል ፡ ብይን ፡ ስለሚቃወምና ፡ በዚህም ፡ ምክንያት ፡ ሕገ-ወጥ ፡ ስለሚሆን ፡ ነው ። [21]

በመንግሥት ፡ ሠራተኞች ፡ የክርክር ፡ አቋምና ፡ በሌሎቹ ፡ ሠራተኞች ፡ የክርክር ፡ አቋም ፡ መከላከል ፡ ያለው ፡ ልዩነት ፡ እንደሚከተለው ፡ ነው ፡ የአሠሪና ፡ ሠራተኛ ፡ ጉዳይ ፡ ቦርድ ፡ በስድሳ ፡ ቀናት ፡ ውስጥ ፡ ክርክሩን ፡ ያልወሰነ ፡ እንደሆነ ፡ ስለተራ ፡ ሠራተኞች ፡ ሆኖ ፡ የሚነጋገር ፡ የሠራተኛ ፡ ማኅበር ፡ ሥራ ፡ ማቋረጥ ፡ ሲችል ፡ ስለ ፡ መንግሥት ፡ ሠራተኞች ፡ ሆኖ ፡ የሚነጋገር ፡ የሠራተኛ ፡ ማኅበር ፡ ግን ፡ የዚያን ፡ ጊዜ ፡ እንኳን ፡ ሥራ ፡ ማቋረጥ ፡ አይችልም ። በተግባር ፡ ላይ ፡ ቦርዱ ፡ የኢንዱስትሪን ፡ ሰላም ፡ ለመጠበቅ ፡ ያለውን ፡ ውሳኔ ፡ በመመርመር ፤ የፊተኛው ፡ የሠራተኛ ፡ ማኅበር ፡ ሥራ ፡ የማቋረጥ ፡ መብት ፡ የተመሠረተበት ፡ ሁኔታ ፡ አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ የሚደርስ ፡ አይመስልም ።

ወደ ፡ መንግሥት ፡ ሠራተኞች ፡ ስንመለስ ፡ ስለ ፡ አሠሪና ፡ ሠራተኛ ፡ ጉዳይ ፡ ከወጣው ፡ አዋጅ ፡ ውጭ ፡ መሆናቸው ፡ አሁንም ፡ ይገጥመናል ። ከአዋጁ ፡ የሠራተኛ ፡ ትርጓሜ ፡ ውጭ ፡ ስለሆኑ ፡ አሠሪያቸው ፡ መንግሥት ፡ ከነሱ ፡ ጋር ፡ ለመ

---

19. ካልተወሰነ ፡ ሥራ ፡ የማቋረጥ ፡ መብት ፡ ጋር ፡ እጅግ ፡ በጣም ፡ የተቃረበ ፡ መብት ፡ ስለ ፡ አሠሪና ፡ ሠራተኛ ፡ ጉዳይ ፡ የወጣው ፡ አዋጅ ፡ ከሠራተኛ ፡ ትርጓሜ ፡ ውጭ ፡ የተተውት ፡ ሰዎች ፡ (ከመንግሥት ፡ ሠራተኞች ፡ ሌላ) ፡ ያላቸው ፡ መብት ፡ ሊሆን ፡ ይችላል ።

20. ቦርዱ ፡ የዳኝነት-መሰል ፡ ተግባር ፡ ሲያከናውን ፡ ውሳኔ ፡ ለመስጠት ፡ ግዴታ ፡ አለበት ፡ ተብሎ ፡ ይገመታል ። ተገቢው ፡ ባለሥልጣን ፡ ሊያስፈጽማቸው ፡ ካልፈቀደ ፡ በስተቀር ፡ ሕጋዊ ፡ መብቶች ፡ ዋጋ ፡ የላቸውም ። የሥራ ፡ ክርክሮችን ፡ በሚነካ ፡ ነገር ፡ ተከራካሪዎች ፡ ጉዳያቸውን ፡ ለግልግል ፡ ሲያቀርቡለት ፡ ተመሳሳይ ፡ ግዴታ ፡ እንዳለበት ፡ ግልጽ ፡ አይደለም ። በሥራ ፡ ክርክር ፡ ጉዳይ ፡ ወገኖቹ ፡ የራሳቸውን ፡ መፍትሔ ፡ እንዲሹ ፡ ሲነግራቸው ፡ ይችላል ፡ ተብሎ ፡ መከራከር ፡ ይቻላል ።

21. አንቀጽ ፡ ሁለት ፡ ደ)፩/(፪)ሠ) ።

ክራክር ፡ ሕጋዊ ፡ ግዴታ ፡ የለበትም ፤ [22] ደግሞም ፡ ከመንግሥት ፡ ጋር ፡ ባላቸው ፡ ክርክር ፡ ላይ ፡ የአሠሪና ፡ ሠራተኛ ፡ ጉዳይ ፡ ቦርድ ፡ ምንም ፡ ሥልጣን ፡ የለውም ። [23] የመንግሥት ፡ ሠራተኞች ፡ ማስተዳደሪያ ፡ ጠቅላይ ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ትእዛዝ ፡ በግል ፡ ወይም ፡ በኅብረት ፡ ክርክር ፡ ፈንታ ፡ ለመላው ፡ የመንግሥት ፡ ሠራተኞች ፡ አንድ ፡ ዓይነት ፡ የሆነ ፡ የደመወዝ ፡ ደረጃ ፡ በሕግ ፡ እንዲወጣ ፡ አዝዟል ። [24] ዳግም በአሠሪና ፡ በሠራተኛ ፡ ጉዳይ ፡ ቦርድ ፡ ፈንታ ፡ የመንግሥት ፡ ሠራተኞች ፡ ማስተዳደሪያ ፡ ጠቅላይ ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ተቋቁሟል ፤ መሥሪያ ፡ ቤቱም ፡ ከገንዘብ ፡ ሚኒስቴር ፡ ጋር ፡ በአንድነት ፡ ሆኖ ፡ የደመወዝ ፡ ደረጃዎችን ፡ ለማውጣት ፡ ኃላፊነት ፡ ተጥሎበታል ። [25]

ላይ ፡ ላዩን ፡ ስንመለከተው ፤ በመንግሥት ፡ ሠራተኞች ፡ ማስተዳደሪያ ፡ ጠቅላይ ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ የደመወዝ ፡ ደረጃ ፡ መውጣቱ ፤ የአሠሪና ፡ ሠራተኛ ፡ ጉዳይ ፡ ቦርድ ፡ በኅብረት ፡ ክርክር ፡ ከሚያደርገው ፡ ውሳኔ ፡ በጣም ፡ የሚለያይ ፡ ላይመስል ፡ ይችላል ። በደመወዝ ፡ ደረጃ ፡ አወጣጥም ፡ ሆነ ፡ በኅብረት ፡ ክርክር ፡ አወሳሰን ፡ አንድ ፡ የተለየ ፡ የመንግሥት ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ለተለዩ ፡ ሠራተኞች ፡ ክፍያቸውን ፡ ወይም ፡ የሥራ ፡ ሁኔታዎችን ፡ ይወስናል ። ሆኖም ፡ በቦርዱ ፡ ፊት ፡ በሚቀርቡት ፡ ጉዳዮች ፡ ሥርዓቱ ፡ በሁለቱ ፡ ወገኖች ፡ መካከል ፡ የሚደረግ ፡ የሙግት ፡ ሥርዓት ፡ ነው ። ተሟጋቾቹ ፡ ወገኖች ፡ እንዲያውቁት ፡ ሊደረግ ፡ የሚያስፈልግና ፡ የመሰማት ፡ ዕድል ፡ ይኖራቸው ፡ ዘንድ ፤ የመሰማት ፡ ሥርዓት ፡ መኖር ፡ አለበት ። [26] ሥርዓቱም ፡ ቦርዱ ፤ በአሠሪና ፡ በሠራተኛ ፡ ማኅበር ፡ መካከል ፡ ላለው ፡ ክርክር ፡ የማያዳላ ፡ ገላጋይን ፡ ቦታ ፡ እንዲይዝ ፡ ተደርጓል ።

የሠራተኞች ፡ ማስተዳደሪያ ፡ ጠቅላይ ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ፡ ስለ ፡ መንግሥት ፡ ሠራተኞች ፡ የሥራ ፡ ሁኔታዎች ፡ አንድ ፡ እርምጃ ፡ ከመውሰዱ ፡ በፊት ፡ የመሰማት ፡ ሥርዓት ፡ እንዲደረግ ፡ አያስፈልግም ። [27] ጽሕፈት ፡ ቤቱም ፡ የማያዳላ ፡ ገላጋይን ፡ ቦታ ፡ እንዲይዝ ፡ በሕግ ፡ ተደንግጓል ፡ ለማለት ፡ አይቻልም ። በብዙ ፡

---

22. በተለያዩ ፡ አያሌ ፡ የክርክር ፡ መንገዶች ፡ እዚህ ፡ መደምደሚያ ፡ ላይ ፡ ሊደረስ ፡ ይቻላል ። ለምሳሌ ፡ (፩) ፡ የመንግሥት ፡ ሠራተኞችን ፡ የወሰድን ፡ እንደሆነ ፤ ስለ ፡ አሠሪና ፡ ሠራተኛ ፡ ጉዳይ ፡ ለወጣው ፡ አዋጅ ፡ አፈጻጸም ፡ መንግሥት ፡ አሠሪ ፡ አይደለም ፤ ምክንያቱም ፡ አሠሪ ፡ ማለት ፡ "ሠራተኛን ፡ ቀጥሮ ፡ የሚያሠራ ፡ ሰው" ፡ ስለሆነ ። (፪) ፡ በመንግሥትና ፡ ለመንግሥት ፡ ሠራተኞች ፡ በሚነጋገር ፡ ማኅበር ፡ መካከል ፡ የሚደረግ ፡ ክርክር ፡ "የኅብረት ፡ ክርክር" ፡ አይሆንም ፤ ምክንያቱም ፡ ይህን ፡ ለመሰለ ፡ ክርክር ፡ ተገቢ ፡ ወገኖች ፡ ስላልሆኑ ፡ ነው ፡ (አንቀጽ ፡ ፳፫) ፡ ደግሞም ፡ "የሠራተኛ ፡ ሁኔታዎችን" ፡ አይመለከትም ፡ (አንቀጽ ፡ ሁለት ፡ ሐ) ፡ መ) ፡ እና ፡ ኀ) ።

23. ቦርዱ ፡ በ"ሥራ ፡ ክርክሮች"ና ፡ "ተገቢ ፡ ባልሆኑ ፡ የሥራ ፡ አፈጻጸሞች" ፡ ላይ ፡ ሥልጣን ፡ አለው ። (አንቀጽ ፡ ፀሥራ ፡ ሁለት ፡ ሀ) ፡ እነሀ ፡ ሐረጎች ፡ የተተለጹት ፡ አሠሪዎችንና ፡ ሠራተኞችን ፡ ብቻ ፡ እንዲመለከቱ ፡ ተደርጎ ፡ ነው ።

24. እላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ፲ ፡ የተጠቀሰው ፡ የመንግሥት ፡ ሠራተኞች ፡ ማስተዳደሪያ ፡ ጠቅላይ ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ትእዛዝ ፡ አንቀጽ ፡ ፳፰(፪) ።

25. ከዚያው ።

26. አንቀጽ ፡ ፲፬ ፡ እስከ ፡ ፲፰ ።

27. አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ በአንድ ፡ የመንግሥት ፡ ሠራተኛ ፡ ላይ ፡ የዲሲፕሊን ፡ እርምጃ ፡ ከመወሰዱ ፡ በፊት ፡ የመሰማት ፡ ሥርዓት ፡ መደረግ ፡ ያስፈልጋል ። እላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ፲ ፡ የተጠቀሰው ፡ የ፲፱፻፶፰ ፡ ዓ ፡ ም ፡ የመንግሥት ፡ ሠራተኞች ፡ ደንብ ፡ ቍጥር ፡ ፩ ፡ ቍጥር ፡ ፺፪ና ፡ የሚከተሉት ። ነገር ፡ ግን ፡ የመንግሥት ፡ ሠራተኞችን ፡ በጠቅላላ ፡ የሚመለከት ፡ ከሆነ ፡ ምንም ፡ የመሰማት ፡ ሥርዓት ፡ አያሻም ።

ረገድ ፡ ያለው ፡ ኃላፊነት ፡ ከግል ፡ አሠሪ ፡ የፐርሶኔል ፡ (ቀጣሪ) ፡ ክፍል ፡ ጋር ፡ የበለጠ ፡ እንዲመሳሰል ፡ ያደርገዋል ። በአሠሪና ፡ በሠራተኛ ፡ ጉዳይ ፡ ቦርድና ፡ በሠራተኞች ፡ አስተዳደር ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ፡ መካከል ፡ በሕግ ፡ ያለው ፡ ልዩነት ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ መዋሉ ፡ ወደፊት ፡ የሚታይ ፡ ነገር ፡ ነው ። የመንግሥት ፡ ሠራተኞች ፡ ማስተዳደሪያ ፡ ጠቅላይ ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ትእዛዝ ፡ ከወጣ ፡ አሁን ፡ አንድ ፡ ስድስት ፡ ዓመታት ፡ ቢሞላውም ፡ የደመወዝ ፡ ደረጃዎች ፡ የመጀመሪያ ፡ ሠንጠረዥ ፡ እስካሁን ፡ ድረስ ፡ በጽሕፈት ፡ ቤቱና ፡ በገንዘብ ፡ ሚኒስትር ፡ በደፋ ፡ (በአፊሴል) ፡ አልታወጀም ። ከዚህም ፡ ይበልጥ ፡ በመንግሥት ፡ ሠራተኞች ፡ በኩል ፡ በጽሕፈት ፡ ቤቱ ፡ ፊት ፡ ስለ ፡ ጥቅማቸው ፡ የሚነጋገርላቸው ፡ ማኅበር ፡ (ድርጅት) ፡ ለማቋቋም ፡ እስካሁን ፡ ድረስ ፡ ጽኑ ፡ ጥረት ፡ የተደረገ ፡ አይመስልም ። የደመወዝ ፡ ደረጃን ፡ በመወሰን ፡ ዓይነት ፡ ነገር ፡ ጠቃሚ ፡ የሆነ ፡ የመሰማት ፡ ሥርዓት ፡ ለማድረግ ፡ የጽሕፈት ፡ ቤቱ ፡ ምኞት ፡ ቢሆንም ፡ እንኳን ፡ እላይ ፡ የተጠቀሰውን ፡ የመሰለ ፡ ማኅበር ፡ እስኪቋቋም ፡ ድረስ ፡ ፈጽሞ ፡ የማይቻል ፡ ይሆናል ።